

# የኮለኔል ባጫ ሁንዴ የህይወት ታሪክ

ኰ/ል ባጫ ሁንዴ አምቦ ጊንጪ ከተማ ተወለዱ። የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል በ1965 (በፈረንጆች አቆጣጠር) ተቀጠሩ። ቀደም ብለው በቴክኒክ ሙያ የሚሰጠውን ትምህርት በግሩም ውጤት የጨረሱት የዚያኔው አፕሬንቲስ ባጫ፤ አየር ኃይሉ በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡና ፍላጎቱ ላላቸው ምልምሎች በሚሰጠው ዕድል ወደ በረራ ሙያ በመዛወር ለተዋጊ በራሪነት የሚያበቃቸውን ስልጠና በማጠናቀቅ የኤፍ - 86 ቀጥሎም የኤፍ - 5E አውሮፕላኖች ላይ ተመድበው ከፍተኛ ውጤትን አስመዝግበዋል።

በ1969 የሶማልያ ተስፋፊ ሰራዊት አገራችንን በእብሪት ሲወር በግምባር ከተሰለፉት ውስጥ ስመ ጥሩው ኰ/ል ባጫ ሁንዴ አንዱ ሲሆኑ በዚህም ጦርነት የሶማልያን የጦር አውሮፕላኖች በአየር ላይ በማራገፍ ስማቸው ከሚጠቀሱትና ለዚህም ወደር የማይገኝለት ጀግንነታቸው የላቀ የጦር ሜዳ ተሸላሚ እንደነበሩ ይታወሳል። ኰ/ል ባጫ ሁንዴ ከ1986 ዓም ከቀድሞው ወታደራዊው ስርዓት ጋር ባለመግባባት የሚያበሩትን ሴሲና አውሮፕላን እያበረሩ ወደ ስደት ኢትዮጵያን በመልቀቅ ሱዳን ገብተዋል።

በመጨረሻም በአሜሪካ የካሊፎርንያ ግዛት በሳን ፍራንሲስኮ ከተማ ህይወታቸው እስካለፈበት ዕለት ድረስ ኖረዋል ። የዚህን ስመጥር ጀግና መኰንን ህልፈተ ህይወት ምክንያት በማድረግ የቀድሞው የመከላከያ ሰራዊት አርበኞች ማህበርና ለመላው የመኰንኑ ቤተሰብና ለአገር ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ መፅፅናናትን ይመኛል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
የቀድሞው የመከላከያ ሰራዊት አርበኞች ማህበር

Ethiomedia.com – September 30, 2015